# ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል

## 24 ኛ ሳምንት

## ገብር ኄር

***ዓላማ***

- ተሰጥዎቻችንን ስለመጠቀም መማር፡፡

***የሚጠና ጥቅስ***

- "ልጄ ሆይ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ፡፡" 2ኛ ጢሞ 2÷1

***ምንባብ***

- ማቴ. 25÷14-30

***መግቢያ***

- ባለፈው ሳምንት ጌታችን ስለ ዳግም ምጽአቱ በተለያዩ ምሳሌዎች ማስተማሩን አይተናል፡፡
- ከነዚህ ምሳሌዎች ስለተማኞች እና ሰነፍ ባርያዎች መስሎ ያስተማረው ይገኝበታል፡፡ ማቴ. 25÷14-30፡፡
- ይህ አንቀጽ በቤተክርስቲያን *"ገብርኄር"* ተብሎ ሲታወቅ የዐቢይ ጾም 6ኛ ሳምንት (ነገ የምንጀምረውም) ከዚህ የጌታችን ትምህርት ተሰይሞአል፡፡
- ገብርኄር - ታማኝ አገልጋይ ማለት ሲሆን፤እግዚአብሔርን በመታመን ስለማገልገል በተሠጠን ተሰጥኦ ተጠቅመን ውጤታማ መሆንና ዋጋውንም እንማርበታለን፡፡

***የትምህርቱ መገለጫ***

- ጌታችን ስለ አንድ ባለጠጋና ባሮቹ ምሳሌ አስተማረ፡፡
- ወደ ሌላ አገር የሚሄድ አንድ ሰው ባሮቹን ጠርቶ ያለውን ገንዘብ ለእያንዳንዱ እንደየአቅሙ፡፡ ለአንዱ አምስት ለአንዱም ሁለት ለአንዱም አንድ፡፡ ሰጠና ሄደ፡፡
- ባለ አምስቱ ሄዶ ነገደና አምስት ፣ ባለ ሁሉቱም ሁለት አተረፈ፡፡ ባለአንዱ ጎን ቆፍሮ ቀበረው፡፡
- ከብዙ ዘመንም በኋላ የእነዚያ ባሮች ጌታ የሠጣቸውን ሊቆጣጠር መጣ፡፡ ባለአምስቱና ባለ ሁለቱ ያተረፉትን ይዘው ሲቀርቡ፡፡ባለ አንዱ ግን ጌታዬ ጨካኝ ብሎ እንደፈራና እንደቀበረውም ነገረው፡፡
- ጌታቸውም ያተረፉትን እያንዳንዳቸውን ***"መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ"*** አለው፡፡
- የቀበረውንም ***"አንተ ክፉና ሃኬተኛ እኔ ካልዘራሁበት እንደማጭድ ታውቃለህን? ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሠጠው በተገባህ ነበር፣ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር፡፡ ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት አሥር መክሊትም ላለው ስጡት"*** አለ፡፡ ወደ ውጪ አውጥተው እንዲጥሉትም አዘዘ፡፡ ***በዚያም ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል***፡፡
- ይህ ምሳሌ ጌታችን ስለዳግም ምጽአቱ ሲያስተምር ተናገረው ነው፡፡ ምሳሌነቱም ባለጠጋው የክርስቶስ፤ ባሮችም ጌታችን በሠጣቸው ጸጋ፣ እውቀት፣ ሀብት፣ መንፈሳዊ በረከቶች የተጠቀሙና ያልተጠቀሙ ሰዎች ምሳሌ ነው፡፡

***ከዚህም ምን እንማራለን?***

- ጌታችን ሲመጣ እያንዳንዳችን በተሰጠን መሠረት እንደሚቀበለንና እንዲሚጠይቀን ለዚህም መዘጋጀት እንደሚገባን እንማራለን፡፡

***ማጠቃለያ***

- ማድረግ የሚገባንን በጠቅላላው እንዲህ ከተገነዘብን የምንፈጽምባቸውን መንገዶች እንይ ፡-

1. **እግዚአብሔር የተለያዩ ስጦታዎችን ሰጥቶናል፡፡** በተፈጥሮ የተሰጠን እውቀት፣በጥምቀትና ሜሮን የተቀበልነው ጸጋ፣ የምንቆርብባትና የምንማርባት ቤተክርስቲያን፣ካህናትና መምህራን፣ የሚወዱንና የሚንከባከቡን ቤተሰቦቻችንና ወዳጆቻችንን በአግባቡ ከተጠቀምንባቸውና ከሰማናቸው ከእግዚአብሔር የተሠጡን ስጦታዎች /መክሊቶችም/ ናቸው፡፡በመጽሐፍ ***"ልጄ ሆይ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ፡፡"*** 2ኛ ጢሞ 2÷1
2. **ተሰጥዎቻችንን እንጠቀምበት** ከላይ በጠቀስናቸውና እውቀታችንን፣ ተሰጥዖችንንና፣ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወታችን በቀና መንገድ ብንመራና ብናሳድግ እግዚአብሔር ***"አንተ ታማኝ በሰላም ወደ ጌታህ ደስታ ግባ"*** ይለናል፡፡በበለጠውም ይሾመናል÷ያከብረናልም፡፡
3. ***ጌታችን ሥራችንን ሊመዝን የሚመጣበት ጊዜ አለ***፡፡ ***"ከብዙ ዘመንም በኋላ የእነዚያ ባሮች ጌታ መጣና ተቆጣጠራቸው፡፡"*** ማቴ. 25÷19 ተብሎ እንደተመሰለ ሁሉንም ስለሥራው ዋጋ ሊሠጥ ጌታችን ይመጣል ***"እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ፡፡"*** ራዕ. 22÷18እንዲል፡፡ስለዚህ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የሚታይ፣ የሚመሠገንም ሥራ ልንሠራና ዋጋችንን ጌታችን እንደሚከፍለን አምነን ልንሠማራ ይገባል፡፡
4. በእድሜአችንም በአግባቡ ከተማርን ፣ ቤተሰብ ከታዘዝና ከተመረቅን በእግዚአብሔር ፊትም በእውነትና በትጋት ካገለገልን፡፡ በነገው ሕይወታችን ***"በጥቂት ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለሁ፡፡"*** ማቴ. 25÷21ና23 እንደሚለን ታላቅ ሰው እንደሚያደርገንም እንማራለን፡፡
5. ***ታዛዥነት*** ሌላው ከዚህ ምሳሌ የምንማረው መታዘዝን ነው፡፡ሁለቱ ሰዎች በተሠጣቸው ታዘው ሲያተርፉ ሦስተኛው ግን ቀብሮ ከመቆየቱም በላይ ለስንፍናው ጌታውን የወቀሰ ነው፡፡ ይሄም የማይታዘዙ አንቢተኛ ልጆችን ይመስላል፡፡ ካለመታዘዝ በትህትና የተባልነውንና የተማርነውን ወደ መፈጸም እንድንመለስ ያስተምረናል፡፡

***ተግባር***

1. የስንፍና ምክንያቶችን ቁረጡ፡፡
2. ታዛገኞች ሁኑ፡፡
3. የተሠጣችሁና ያላችሁን በረከት እወቁ! እግዚአብሔርን አመስግኑበት! አድንቁ! ተጠቀሙበትም፡፡

***መዝሙር***

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ይጠብቀኛል
በዕረፍት ውሃ በለምለም መስክ እኔን ይመራኛል፡፡

**ይቆየን፡፡**

**አዘጋጅ፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ እና ዲ. ዮናታን ኢያሱ**